# ጠላቶች ካይደሉ ነፍሰ ገዳይ ደመኞች ናቸው

ከጌታቸው ኃይሌ

“ወያኔ ጠላት ነው ወይስ አይደለም?” የሚለው ጥያቄ እንደትልቅ ጉዳይ ዋና መወያያ ሆኖ ሰንብቷል። ወይ ጉድ! አንድ ሰው ተነሥቶ፥ “ወያኔ ጠላት ነው” ሲል ግማሹ ያጨበጭባል፤ ግማሹ ይናደዳል። ሌላው ተነሥቶ፥ “ወያኔ ጠላት አይደለም” ሲል፥ ቅድም ያጨበጨበው አሁን ይናደዳል፤ የተናደደው ያጨበጭባል። ወይ ጉድ! ሁላችንም ወያኔ ጠላት ነው ወይም አይደለም በሚለው አስተያየት ወይም ፍርድ ላይ ተስማምተን የተማማልን ይመስል፥ የተለየ ሐሳብ ያለውን፥ “እንዴት እንዲህ ሳከብርህ ወያኔ ጠላት ነው/ አይደለም ትላለህ?” እያልን ወደትዝብት፥ እንዲያውም ወደመለያየት እንሄዳለን። የመለያያ ባለጸጎች ሆነን ሳለ፥ መለያያ እንደቸገረው ሰው መለያያ ቢወድቅልን እያልን የሰው አፍ ወይም ብዕር እንጠባበቃለን። ወያኔ ስንት ኢትዮጵያውያን/ት እየፈጀ፥ ስንቶቹን በእስር ቤት እያማቀቀ የሚፈጽመውን የወንጀል ሥራ ከሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶች መዝገብ እያወጣሁ ብዘረዝርም፥ “ወያኔ ጠላት ነው” ካላልኩ ዝርዝሩን ጎርጉሬ ማውጣቴና ማመኔ ዋጋ የለውም፤ ወዳጅ አጣለሁ። በዚያው አንጻር፥ ወያኔ መንገድ ይሠራል፤ ትምህርት ቤት ይከፍታል፤ ንግድ ያበረታታል፤ ነፃ ጋዜጣ እንዲታተም ይፈቅዳል፥ እያልኩ በጎ ሥራውን አሳይቼ፥ “ግን ወያኔ ጠላት ነው” ብል ብዙ ወዳጅ ላፈራ ነው። ወይ ጉድ! እስቲ አሁን ይኸ አስተሳሰብ ልክ ነው? እንዴት ልክ ሊሆን ይችላል?

የወያኔን ወንጀል ዘርዝሮ፥ “ወያኔ ጠላት አይደለም” የሚለውም፤ “ጠላት አይደለም” ሲባል የሚያዝነውም ሁለቱም አስተሳሰባቸው አይገባኝም። በእኔ አስተሳሰብ ወያኔ የኢትዮጵያ ጠላት ነው፤ ልጆቿን የሚያሰቃይ በእናትየዋ ዘንድ ጠላት ላይሆን አይችልም። ግን የወያኔን ወንጀል የሚቀበል ሰው፥ “ወያኔ ጠላት ነው” ቢልም ባይልም፥ ወያኔን ለማስወገድ ከተሰለፈ፥ የግል አስተያየቱን ለግሉ ትቼ አብሬው እሰለፋለሁ። ጽድቅንና ፍርድን ለይተን ማወቅ አለብን። ጽድቅ የምለው በእንግሊዝኛ fact የሚባለውን ነው። ጽድቅ (fact) እውነት ነው፤ አይለዋወጥም። ፍርድ ግን አስተያየት (opinion) ነው፤ ሊለዋወጥ፥ በየቤቱ ሊለያይ ይችላል። ማንም ሰው ጭንቅላቱ በፈቀደለት ልክ የራሱ አስተያየት፥ የራሱ ፍርድ ይኖረዋል። ያ አስተያየት ጥሩ መሆን አለመሆኑ የሚታወቀው ጊዜ ሲፈተነው እንጂ በደፈናው ከራስ አስተያየት አነጻጽሮ፥ “ከአንተ አስተያየት የእኔ አስተያየት ይሻላል” በማለት አይደለም። ጽድቅ ግን መፈተን የማያስፈልገው፥ ጊዜ ሳይደፍረው፥ ሳይለዋወጥ የሚኖር ነገር ነው፤ የሚክደው ዋሾ ብቻ ነው። “ወያኔ የኢትዮጵያን ልጆች አያስሠቃይም፤ የምርጫ ድምፅ አልሰረቀም” የሚል ጽድቅን የሚጋፋና የሚክድ ዋሾ ነው፤ ዋሾ ዋሾ፥ የወያኔ ውሾ።

“ወያኔ ጠላት አይደለም” ማለት ግን ጽድቅ ሳይሆን አስተያየት ነው። እንዴት አስተያየት ሊሆን ይችላል? አስተያየትስ አስተያየት ነው፤ መጠየቅ ያለበት፥ “ነፍሰ ገዳይን እንዴት ጠላት አይደለም ከሚል አስተሳሰብ ላይ ሊደረስ ይቻላል?” የሚለው ነው። እኔም ግር ስላለኝ ጥቂት ጊዜ ወስጄ አሰቤበታለሁ። ነገሩን ለማሰብ የሰጠሁት ጊዜ ጥቂት የሆነው፥ ከላይ እንደተናገርኩት አሳሳቢ ጉዳይ ስላይደለ ነው። አሳሳቢ ሊሆን የሚችለው ጽድቁ ቢካድ ነበር፤ ከእኛ ወገን ሆኖ ጽድቁን የካደ እስካሁን አላጋጠመኝም። የአንድነታችን መሠረቱ አልተናጋም፤ በዚህ ደስ ሊለን ይገባል። የወያኔን ነፍሰ ገዳይነት ያመነ ሰው ወያኔ ጠላት አይደለም ካለ፥ ምክንያት ቢኖረው ነው። “ምክንያት ቢኖረው ነው” ብለን ብንደመድምና እዚህ ላይ ብናቆም ተገቢ ነው፤ ግን ጉዳዩ ብዙ ስላነጋገረ እስቲ ለወሬ ያህል ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉትን በግምት እንደርድራቸው፤ ግምት ስለሆኑ ማንንም አይመለከትምና፥ ይኸ የእገሌ ምክንያት ነው እንዳንል ላስጠንቅቅ፤ ሌላው ቢቀር የእገሌ ነው እያልኩ አለማቅረቤን ላስታውስ።

ጠላት ማነው? በሚለው ጥያቄ እንነሣ። ጉዳዩ በአሁኑ ሰዓት ምን ሊጠቅም ተነሣ? የሚለው ጥያቄም አብሮ ይሄዳል። ወያኔ ጠላት ካልሆነ ጠላት የሚባለው ምን ሥራ የሚሠራ ሰው ነው? ምናልባት በኢጣልያ መወረራችን የጠላትን ትርጒም ለውጦብን ይሆናል። አምስቱ ዓመት የኢጣልያ አገዛዝ “የጠላት ዘመን” ነው የሚባለው። ማንም የውጪ ወራሪ ሲነሣ፥ “ጠላት መጣ” ነው የሚባለው። በዚህ አነጋገር “ጠላት” የሌላ ሀገር ሰው (ቅኝ ገዢ) ነው። በዚህ አነጋገር፥ የሌላ ሀገር ሰው ከአጠቃ ጠላት ነው፤ አጥቂው የሀገር ልጅ ከሆነ ጠላት ላይሆን ነው። ወያኔዎች ኢትዮጵያውያን/ያት የትግራይ ልጆች ስለሆኑ፥ “ጠላት” አይደሉም፤ ማለት፥ ትግራይን እንደኤርትራ የራሷ መንግሥት ያላት ሌላ

ሀገር እስካላደረጓት ድረስ፥ ቅኝ ገዢዎች አይደሉም:: ግን ጠላት ሁል ጊዜ ቅኝ ገዢ የውጪ ዜጋ አይደለም:: ጠላት ማለት ደግ ነገር የሚጠላ ነው:: ሰይጣን ጸላኤ ሠናያት ("ደግ ነገር የሚያስጠላው" ፍጡር) ይባላል፤ ጠላትነቱን የሚገልጸው በሰው ልብ አድሮ፥ ሰውን እየጋለበ እንጂ ራሱ በገሃድ ተገልጦ አይደለም:: ሔዋንን ያሳሳታት በእባብ ልብ አድሮ፥ እባብን እየጋለበ ነው:: ያ የእባብ ተንኮል የሚገለጥበት ሰው ሁል ጊዜም የውጪ ሀገር ሰው አይደለም፤ ጎረቤት፥ ወዳጅ፥ ወንድም፥ ባል ጠላት ሊሆን ይችላል፤ ሰይጣን ይጋልበዋል ይባላል:: ቅዱስ ዳዊት ልጁ አቤሴሎም ሊያጠፋው በተነሣበት ጊዜ ከጠላቴ አድነኝ ብሎ ጸልይዋል::

ጠላት የውጭ ሰው ብቻ ቢሆንማ በማን ዕድል!! ያስተባብረን ነበር:: ወያኔ ራሱ የውስጥ ጠላት መሆኑ አልበቃ ብሎት ሌሎች የውስጥ ጠላቶች ይኮተኩታል:: በምርጫ እንዳይሸነፍ ከሚያደርገው የፕሮፓጋንዳ ውርጂብኝ ብዙ ነገር አይተናል:: ለምሳሌ፥ "በኮንስቲትወንሲ ግንባታ" ጊዜ "በአጋርነት የቆሙ ክልሎች ብሔር-ብሔረሰብ ተወላጆችን (የሶማሌ፥ ሐረሪ፥ ጋምቤላ፥ አፋር፥ ወዘተ.) ስብስብ በመረጃ መደገፍ፥ የእንቅስቃሴ አቅጣጫዎችን በማመላከት ባሉበት (የውጪ) አገር (ሆነው) የትውልድ አገራቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ እንዲቆሙ (advocacy) ማድረግ" አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል:: "በመረጃ መደገፍ" ማለት "እናንተን የማይመስሉ ገዢዎች (አማሮች) ይበድሏችሁ ነበር፤ ፖለቲካው "ከእኛ መብት ከሰጠናችሁ ጋር ቁሙ" ማለት መሆኑ ግልጽ ነው:: አለዚያማ እነዚህ "ጭቁን" ኢትዮጵያውያን ለምን ተለይተው ተዘረዘሩ? "ጠላት ምን ብጤ ነው?" ለሚለው ጥያቄ መልሱ ያከራክር ይሆናል እንጂ፥ በሀገር ውስጥ ጠላት መኖሩስ አያከራክረንም:: ያም ሆኖ፥ ወያኔዎችን ጠላት ማለት የሚያከራክር ከሆነ ደመኛ እንበላቸው:: ደም የተቃቡትን ደመኛ ማለት ባህላዊ አነጋገር ነው፤ የግድ የውጪን ዜጋ፥ የውጪን ቅኝ ገዢ አያመለክትም:: **ወያኔዎች ነፍሰ ገዳይ የኢትዮጵያ ደመኞች ናቸው::** እነሱ በሥራቸው ሳያፍሩ፥ እኛ ሥራቸውን መመዝገብ አያሳፍረንም::

ሌላውን ምክንያት ወደመፈለግ ልሂድ፤ "ወያኔ ጠላት አይደለም ማለት የፖለቲካ ብስለት ነው" የሚሉ አሉ:: እንዴት ሲሏቸው፤ "ወያኔን ጠላት ከአደረግነው ሊደራደር አይፈልግም፤ ካልተደራደረ ኢትዮጵያን አይለቅም፤ 'ጠላት ከአደረጋችሁኝ በጠላትነቴ እጸናለሁ፤ ልታጠፉኝ ስለምትፈልጉ ጨክኜ እንደመዥገር ተጣብቄ እቀራለሁ፤ ከተሸነፍን አማሮች ይፈጁናል፤ የሚያዋጣን በስልጣን መቆየቱ ብቻ ነው' እያለ ትግሬዎቹን ይደልላቸዋል" ይላሉ:: ወያኔን ጠላት አይደለም ሲሉት ልቡ ራርቶ ለኢትዮጵያ ነፃነትን የሚሰጥ ቢሆን፥ ጠላት ነው ማለት ቀርቶ አፍቃሬ ኢትዮጵያ ነው እያልን እንለፍፍለት፥ "ሰላም ከዝክረ ስምከ ርኅሩኅ ልብ ወያኔ፤ በውሳጤከ ዘአልቦ ሚያኔ" እያለ ውዳሴ ወያኔ ደራሲ ደብተራ እናስፈልግለት ነበር:: ግን ማንንም ሳይፈሩ፥ ሳይገላመጡ ከዓሥራ ሰባት ዓመት በላይ ማንነታቸውንና ምን እደሚፈልጉ በገሃድ ከነገሩንና ከአሳዩን በኋላ፥ ጥሩ ሰዎች መሆናችንን ብናሳያቸው ኢትዮጵያን ዲሞክራሲያዊት ያደርጋሉ ማለት ራስን መደለል ነው:: እንደ መፈክሩ ከሆነ *ምንም ቢለማመጡት የትግሬ ጭራቅ፥ በገዛ ፈቃዱ አይልም ፈቀቅ*፡ ሰሚ ጆሮ ኖሮት ያልሰማ እንዳለ ይስማ! **ወያኔዎች ኢትዮጵያን በፈቃዳቸው አይለቁም::** ተቃዋሚ ቡድኖች በትግሉ መጽናታቸው ለኢትዮጵያ ታላቅ ተስፋ ነው:: ግን ገፍታሪ አዲስ መላመምታት ሊኖርባቸው ነው::

ሶስተኛ ምክንያት ፈልጌ ላቁም፤ አንድ ሰው አንዱን ድርጅት ወይም ሌላውን ሰው "ጠላቴ ነህ" ካለው፥ በዚያው አያይዞ "እኔም ጠላትህ ነኝ" ማለቱ ነው:: እንዲህ አፉን አውጥቶ፥ "ጠላትህ ነኝ" ባይለውም "ጠላቴ ነህ" ካለው እሱም ያንን ሰው ጠላቱ ማድረጉ አይቀርም:: ሲጠሉት የሚወድ ክርስቶስና ቃሉን የሚያከብሩ ምእመናን ብቻ ናቸው:: ጓደኞቻቸውን በሕይወት የሚቀብሩ ደቂቀ ኤንቨር ሆጃ (ወያኔዎች) በሃይማኖተኝነት ስለማይታሙ፥ እንኳን "ጠላቴ ናችሁ" ያላቸውንና ቀና ብሎ ያላያቸውን ሳይቀር አማራ በመሆኑ ብቻ በጠላትነት ይፈርጁታል:: እንግዲህ፥ "ጠላቴ ናችሁ" ያላቸውን ጠላታቸው ከአደረጉት፥ እሱና እነሱ ተፈላላጊዎች (አጥፊና አጥፊ፥ ጠፊና ጠፊ) ይሆኑና በሰላም በአንድ ከተማ ሊኖሩ አይችሉም:: ሁሉም የሚያስኬደውን መንገድ እየፈለገ ጠላቱን ያጠቃል:: በዚህ ሁኔታ ወያኔን መቋቋም አይቻልም፤ መንግሥቱ የነሱ ነው፤ ፖሊሱ የነሱ ነው፤ የደኅንነት ሰዎች ቀን በቀን የፈለጉትን ገድለው፥ የፈለጉትን ጎትተው ይዘውት ይሄዳሉ፤ ወስደው አውሬነታቸውን ሲያሳዩት እሱን አያርገኝ፤ ዳኛው የነሱ ነው፤ ወያኔዎቹ የሚፈልጉትን ፍርድ ጽፈው ይልኩለታል፤ ወይም ራሱ ሄዶ ያመጣል:: ስለዚህ የሚያዋጣ የሚመስለው ዘዴ ወያኔን የኢትዮጵያን ልጆች ነፍሰ ገዳዮች መሆናቸውን በሰብአዊ መብት ድርጅቶች አስመስክሮ፥ "የኢትዮጵያ ጠላት አይደላችሁም" ማለቱ ነው:: ይህ ዘዴ ማንነታቸውን አሳውቆ አብሮ በአንድ ከተማ ለመኖር፥ ከኢትዮጵያ ወጥቶ ተመልሶ ወደኢትዮጵያ ለመግባት ያስችል ይሆናል:: መጥፎነቱ ከምኑ ላይ ነው? እንዲህ ከሆነ፥ እኔም አብሬ፥ "ወያኔ ጠላት አይደለም?" እላለሁ::